## ማጠቃለያ

- **የሪፖርቱ ግብ:** የሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የተማሪዎችን ምዝገባ ማሽቆልቆል አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ነገሮች ለመረዳት፣እንዲሁም እነዚህ ነገሮች የትምህርት ዲስትሪክቱ ለወደፊት ዘላቂ፣ከፍተኛ ጥራት ያለው እና ፍትሃዊ ትምህርት በመስጠት ላይ ያላቸውን አንድምታ ለመረዳት።
- **የጥናቱ አጋሮች:**የሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች የምዝገባ እቅድ ቡድን፣ስትራቴጂ 360 የጥናት ድርጅት (research firm Strategies 360) እና የMIT's Blueprint Labs ተመራማሪዎች፣የፖሊሲ ጥናት ላብራቶሪ
- **የጥናቱ ዘዴዎች:** 1) በየተንከባካቢዎችን ተወካዮች የዳሰሳ ጥናት ተድርጓል፤)በሲያትል፣በአጎራባች ዲስትሪክቶች እና መሰል ከተሞች የተማሪዎችን የምዝገባ ማሽቆልቆል አዝማሚያዎች ተተንትነዋል፤እና 3) እንደ የተንቀሳቃሽ ቤተሰብ መረጃ ካሉ ውጫዊ ሁኔታዎች መረጃ ተተንትነዋል።
- **የዳሰሳ ጥናቱ መረጃ:** Strategies 360 በጾታ፣በዘር እና በጂኦግራፊ የቀድሞ እና የአሁን ተማሪዎች ተንከባካቢዎች ተወካዮች የዳሰሳ ጥናት (በእንግሊዘኛ፣በስፓኒሽኛ፣በካንቶኒዝኛ፣በቬትናምኛ፣በሶማሊኛ እና በአማርኛ የቀረበ) አካሂዷል።በሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ትምህርታቸውን ተምረው በማያውቁ ተማሪዎች ተንከባካቢዎች የዳሰሳ ጥናት ተካሄዷል።በዋጋ እና በአዋጭነት ገደቦች ምክንያት ሁሉም የዳሰሳ ጥናቶቹ ተሳታፊዎች በሲያትል ሚኖሩት ናቸው።ወደ 125,000 የሚጠጉ አዋቂዎች የዳሰሳ ጥናቱን እንዲሞሉ ተጠይቀው የ 1,420 ምላሾችን ተሰብስቧል።

## ቁልፍ ግኝቶች

### የዳሰሳ ጥናቱ ውጤቶች አጠቃላይ እይታ

- **በሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ደስተኛ የሆኑ:** አሁን ካሉ ተማሪዎች መካከል 86% የሚሆኑት በሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች ደስተኞች ናቸው።66% የቀድሞ ተማሪዎች እና 53% በሲያትል ትምህርት ቤቶች ተምረው የማያውቁ ተማሪዎች በሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች ደስተኞች እይደሉም።
- **ሰዎች ስለ ሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የሚወዷቸው** (በስርጭት ቅደም ተከተል፣ከአሁን እና ከቀድሞ ተማሪዎች ጋር ተመሳሳይ ነው):የባለቤትነት እና የማህበረሰብ ስሜት፣ታታሪ እና አሳቢ አስተማሪዎች ፣ እና ትምህርት ቤቱ ወደ ቤት ያለው ቅርበት
- **ሰዎች ስለ ሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የማይወዷቸው** (በስርጭት ቅደም ተከተል፣ከአሁን እና ከቀድሞ ተማሪዎች ጋር ተመሳሳይ ነው)**:**የትምህርት እና የስርዓተ-ትምህርት ጥራት፣የመማሪያ ክፍሎች መጨናነቅ፣የገንዘብ እጥረት እና መጨናነቅ ስጋት
- **ምዝገባ ሊቀንስባቸው የሚችሉ ምክንያቶች** (አሁን ባሉ ተማሪዎች ዘንድ እንደ ቅደም ተከተላቸው።ስለ የትምህርት ጥራት፣የተሻለ  አማራጭ የመኖር፣የደህንነት እጦት ስሜት እና አሁን ስራ ላይ ያለውን ስርዓተ ትምህርት ስጋት
- **የሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የወደፊት ቅድሚያ የሚሰጣቸው በጣም አስፈላጊ ነገሮች** (አሁን ባሉ ተማሪዎች መካከል ያለው ስርጭት በቅደም ተከተል):የመማርያ ክፍል ተማሪዎች መጠን በመቀነስ እና የትምህርት ቤት ስራዎች በማሻሻል የትምህርት ጥራትን ማሻሻል እና የገንዘብ ድጋፍ መጨመር
- ከአምስቱ ሁለቱ የቀድሞ ተማሪዎች ተንከባካቢዎች በሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች ዳግም ለመመዝገብ እንደማያስቡ ተናግሯል።**በድጋሚ ለመመዝገብ የበለጠ ፍላጎት** ያላቸው በድጋሚ ለመመዝገብ  ከሌሎቹ ምክንያቶች በበለጠ ያቀረቡት ምክንያት የአካዳሚክ ጥብቅ ማሻሻያዎች እንደሆነ ጠቅሰዋል።


### የምዝገባ መቀነስ አመልካቾች

- **የኪንደርጋርተን ክፍል መቀነስ:** ከ2012 ጀምሮ በሲያትል ተወልደው ወደ ኪንደርጋርተን የሚገቡ ልጆች መጠን በከፍተኛ ሁኔታ ቀንሷል።የኪንደርጋርተን ክፍሎች በቀጣይነት እየቀነሱ ነው: የ2023 የኪንደርጋርተን ቡድን 3,714 ተማሪዎች ነበሩ፣ከኮቪድ በፊት የነበረው አማካኝ የኪንደርጋርተን ቡድን መጠን ደግሞ 4,668 ተማሪዎች ነበሩ።ይህ እየቀነሰ ያለውን የኪንደርጋርተን ክፍሎች ለአብዛኛዎቹ የሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የምዝገባ ማሽቆልቆል ምክንያት ነው።

- **ልጆች ያሉባቸው ቤተሰቦች መቀነስ:** ከ2017 ጀምሮ በሲያትል ውስጥ ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦች በ16% ቀንሰዋል።ከእነዚህ ከሲያትል ከወጡ ልጆች ካሏቸው ቤተሰቦች 70% ያህሉ ከስቴቱ ወጥተዋል፣15% የሚሆኑት ደግሞ በኪንግ ካውንቲ ውስጥ ወደ ሌላ ቦታ ተዛውረዋል።

## ለተማሪዎች ምዝገባ ማሽቆልቆል ጉልህ አስተዋፅዖ ያላደረጉ ነገሮች

- **ዲስትሪክቱ የሚለቁትን ተማሪዎች መቶኛ የተረጋጋ ሆኖ ቆይቷል:** ከ2011 ጀምሮ ዲስትሪክቱን የሚለቁ ተማሪዎች በመቶኛ ከጠቅላላ ምዝገባ በ5% እና 7% መካከል ይቀያየራል።




- **የግል ትምህርት ቤት የተማሪዎች ምዝገባ ለውጥ:** በ2019 እና 2023 መካከል፣በመላ ኪንግ ካውንቲ (ሲያትል ጨምሮ) የግል ትምህርት ቤት ምዝገባ በ3,182 ተማሪዎች ጨምሯል።በዚሁ ወቅት፣11,131 ተማሪዎችን ከሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ለቋል።የኪንግ ካውንቲ እያንዳንዱ አዲስ የግል ትምህርት ቤት ተማሪ ከሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የመጣ ቢሆንም፣ይህ የሚያሳየው በኮቪድ ወቅት ዲስትሪክቱን ለቀው ከወጡት ተማሪዎች 25% ብቻ ነው።

## የዘር እኩልነት ተፅእኖዎች

- ጥቁር፣የአሜሪካ ነባር ተወላጅ እና የፓሲፊክ ደሴት ተማሪዎች ከላቲኖ፣ከብዙ ዘር እና ነጭ ተማሪዎች በበለጠ ከዲስትሪክቱ ለቀዋል።
- ገቢ መሰረት በማድረግ የሚሰጡ ባለ ሁለት መኝታ ቤቶች ከፍተኛውን የሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ያስመጣሉ።ነገር ግን፣ቤተሰብን ያገናዘበ ተመጣጣኝ መኖሪያ ቤት በመግኘት ላይ ጉልህ የሆነ እጥረት አለ።

# ቀጣይ እርምጃዎች እና የሚመከሩ እርምጃዎች

ሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የተማሪዎችን ምዝገባ ማሽቆልቆልን በመዋቅራዊ መነፅር መፍትሔ አቅርበዋል--ተማሪዎች፣ቤተሰቦቻቸውን እና ማህበረሰባቸውን በተሻለ ሁኔታ የሚደግፍ ስርዓት እንዴት መፍጠር እንችላለን?ለዚህ ግኝቶች ምላሽ የሚሰጡ ምክሮችን እንሰጣለን።

- በሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ለኪንደርጋርተን እና ከዚያም በላይ የሚመዘገቡትን ልጆች መቶኛ ለመጨመር፣ከቅድመ መደበኛ ትምህርት ተማሪዎች ጋር በመገናኘት ላይ ማተኮር፣ማለትም ከየ pre-K ተማሪዎች ተንከባካቢዎች እና የpre-K እና የሕጻናት እንክብካቤ አጋሮች።
- ከሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች ማህበረሰብ ጋር በስርአተ ትምህርት እና በትምህርት ዙሪያ መወያየት።
- ያልተቆጠሩ ተማሪዎችን ማግኘት እና በሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች እንደገና እንዲመዘገቡ ማድረግ።
- ለተወሰኑ የቀለም ተማሪዎች ቡድን ከሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የሚለቁበትን ምክንያት አስመልክቶ የሚያወያይ ከተማሪዎች፣ከቤተሰቦች እና የማህበረሰብ አባላትን ያካተተ ግብረ ኃይል መፍጠር።

- የቤተሰቦች የመኖሪያ ቤቶች አቅርቦትን ለመፍታት ከከተማ ኤጀንሲዎች ጋር መተባበርን መቀጠል።
- በቅርብ ዓመታት ውስጥ እንደ Minneapolis እና Atlanta ያሉ ዲስትሪክቶች እና ከተሞች የተማሪዎችን ምዝገባ እንዴት መጨመር እንደቻሉ ለማወቅ ተጨማሪ ጥናት ማካሄድ።